# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ሚያዚያ 15 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**በሀገሪቱ በተከሰተ ርሀብ ዜጎች እየሞቱ መሆኑ ታወቀ፤**

**በህዝቡ ላይ አዲስ ከፍተኛ የመብራት ታሪፍ ሊቆለልበት መሆኑ ተጋለጠ፤**

**ወያኔ በአባይ ግድብ ላይ ጥናት እንዳላደረገ ባለስልጣኑ አመነ፤**

የወያኔ ቡድን የደረሰበትን የፖለቲካ ኪሳራ ለመጠገኛ ይረዳው ዘንድ ምንም ጥናት ሳይደረግበት በግብታዊነት ብቻ አባይ ግድብን እገነባለሁ እያለ እየወተወተ ባለበት በዚህ ወቅት በሀገሪቱ እጅግ አስደንጋጭ እልቂት መከሰቱ ተጋለጠ::

በመለስ ዜናዊ የሚመራው አረመኔው የወያኔ ቡድን ቅድሚያ የዜጎችን ህይወት መታደግ ሲገባው የደረሰበትን የፖለቲካ ኪሳራ ለመጠገን ሲል ብቻ በሌለና ባልተፈጠረ ነገር ላይ የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር እየተንደፋደፈ ባለበት በዚህ ግዜ እጅግ አስከፊና አስደንጋጭ ርሀብ ተከስቶ ዜጎች እንደ ቅጠል እየረገፉ ለቀባሪ ያስቸገሩበት ደረጃ ላይ መድረሱን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጦል::

ሁሌም ልምለሜ በማይለየው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው የዝናብ እጥረት ሳቢያ በተከሰተ ድርቅ ከ5 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ዜጎች በርሀብ እየተሰቃዩ ሲሆን ሰዎችና ከብቶቻቸው እየሞቱ ቀባሪ አጥተው አካባቢው በበሽታ እየተበከለ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተው አስከፊ ርሀብ ምክንያት የተነሳ ቁጥራቸው የበዛ አርብቶ አደሮች ቀዬአቸውን ጥለው እየተሰደዱ ቢሆንም በዚያም ተመሳሳይ ድርቅ በመከሰቱ ለከፋ ችግር ከመዳረጋቸውም በላይ ህፃናት ልጆቻቸው ርሀቡን መቁዋቁዋም ተስኖዋቸው እየሞቱባቸው እንደሚገኝም ተገልፆዋል::

በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ቦረና እና አካባቢው በተከሰተ ርሀብ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ ዜጎች እያለቁ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀባሪ አጥተው እንደሚገኙ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ይህን የመሰለ አስከፊ ችግር በዜጎች ላይ እየደረሰ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ ደብቆና ሸፋፍኖ ህዝቡ እንዳያውቅ ቢያደርግም በቅርቡ ግን ተጋልጦ አደባባይ ሊወጣ እንደቻለም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

የሚደርስላቸው አጥተው ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሁለት እና ከዚያም በላይ ህፃናት እና አሮጊት እናቶች እየሞቱ እንደሚገኙ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ወያኔ ለዜጎቹ ትኩረት ነፍጎ በአባይ ላይ ብቻ እየጮኸ መገኘቱ ብዙ ዲፕሎማቶችን ጭምር እንዳሳዘነ ታውቆዋል::

የተጣቂ የተቃዋሚ ኃይሎች ይንቀሳቀሱበታል ተብሎ በወያኔ በኩል ትልቅ የስጋት አቅጣጫ እንደሆነ የሚነገርለት ይሄው የደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ርሀቡ ከሁለት ወራት በፊት አንደተከሰተ ባለስልጣናቱ ቢያውቁም በምስጢር ሸፋፍነው በማቆየታቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለሞት ሲዳረጉ በሚለዮኖች የሚቆጠሩት ደግሞ ለከፋ ችግር ተዳርገው በሞት እና በህይወት መሀከል እንደሚገኙ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ዙሪያ ገባውን በፖለቲካ ትኩሳት ተወጥሮ ያለው ይሄው አምባገነን ቡድን ሰሞኑን በጀመረው በአባይ ግደብ ቅስቀሳ ሸፍኖ ለማቆየት ብዙ ጥረት ሲያደርግ ቢቆይም አንድ የአለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅት በቦታው በመገኘት ሁኔታውን በማየቱ ምስጢሩ ሊጋለጥ እና ህዝብ ሊያውቀው እንደቻለም ታውቆዋል::

በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የታጣቂ ተቃዋሚ ኃይሎች ደጋፊ ናቸው ተብለው ከዚህ ቀደም ሲታሰሩና ሲገረፉ የኖሩት እነዚሁ የቦረና ዞን ነዋሪዎች እና ተወላጆች ዛሬ በድርቅ ሳቢያ በተከሰተ ርሀብ እንደ ቅጠል እየረገፉ ባለበት ወቅትም በጥይት ተኩሶ ከመግደል ባልተናነሰ ሁኔታ እርዳታ እንዳይደርስላቸው ተደርጎ በምስጢር ተይዞ ብዙ ዜጎች እንዲያልቁ መደረጉም ታውቆዋል::

በአሁኑ ሰዓት ከ5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በሞት አፋፍ ላይ ባለበት...... በርሀብ እየተሰቃየ ህፃናት እና አዛውንት አሮጊቶች እየሞቱ የሚቀብራቸው በጠፋበት ....... የአለም አቀፍ ድርጅቶች ለዜጎቻችን ትኩረት ሰጥተው እየተሩዋሩዋጡ ባለበት ወቅት የወያኔ ቡድን ሰምቶ እንዳልሰማ...... አይቶ እንዳላየ....... አውቆ እንዳላወቀ .......በመምሰል ለጊዜያዊ የፖለቲካው ፍጆታ ሲል ብቻ ሊሆን በማይችል ነገር ላይ

የህዝቡን ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር እየዘለለ መገኘቱ ለሀገሪቱ ዜጎች ደንታ እንደሌለው የሚያሳይ ነው ተብሎዋል::

ከጥር ወር ጀምሮ የርሀብ አደጋው እንደሚከሰት አስቀድሞ ሲያጠኑና ሲከታተሉ የነበሩ ለጋሽ ድርጅቶች ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጭምር ጥቆማ የሰጡ ቢሆንም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በመተው ዛሬ ዜጎች እንደ ቅጠል በየቦታው እየረገፉ ይገኛሉ::

ለተራቡት ወገኖች የእርዳታ እህልና ገንዘብ ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ቢመጣም እህሉን ወደብ ላይ እየሸጠ ገንዘቡን ደግሞ ለጦር መሳሪያ እያዋለ የተራቡት ዜጎች ለሞት እና ለስቃይ እየተዳረጉ እንደሚገኝም የእርዳታ ድርጅት ሰራተኞች በመረጃ አስደግፈው ይገልፃሉ::

በአሁኑ ሰዓት አስቸኩዋይ እርዳታ እንዲደረግላቸው የለጋሽ ድርጅት ሰራተኞች ጥሪ እያቀረቡ ቢሆንም የወያኔ ቡድን ግን ሁኔታውን እንደ ተራ ነገር በመቁጠሩ እስከ አሁን ድረስ ዜጎች አንዳችም ድጋፍ ያልተደረጋቸው መሆኑም ታውቆዋል::

ከዕለት ወደ ዕለት የወያኔ የግፍ አገዛዝ እየከፋና እየሰፋ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የኑሮ ውድነቱ ጣራ እየነካ ህዝቡ እጅግ ከባድ ፈተና ውስጥ ገብቶ ባለበት በዚህ ግዜ አዲስ የመብራት ታሪፍ ጭማሪ ሊያደርግ መሆኑ ደግሞ አስገራሚ ሆኖዋል::

የኑሮ ውድነቱ ህዝቡን አላላውስ ብሎ የስንግ ይዞት ባለበት በዚህ አንገብጋቢ ወቅት ህዝቡ የእለት ጉረሮ መድፈን አቅቶት እየተንገላታ መሆኑ እየታወቀ የወያኔ ቡድን በመብራት ታሪፍ ላይ አስደንጋጭ ጭማሪ ሊያደርግ መዘጋጀቱም እያነጋገረ መሆኑ ታውቆዋል::

በኑሮ ውድነቱ አስቀድሞ ተሸመድምዶ ያለው ህዝብ የተጫነበትን ሸክም ሳያቃልል እንደገና ሌላ ተጨማሪ ሸክም ለመጫን እየተራወጠ የሚገኘው ይሄው አረመኔ ቡድን ሰሞኑን በአዲስ መልክ የመብራት ታሪፍ ለመጨመር ጥናቱን ማጠናቀቁን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ሾልኮ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

ተደረገ የተባለው ይሄው አዲሱ የመብራት ታሪፍ ጭማሪ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ህዝቡ መክፈል ከሚችለው አቅም በላይ እንደሆነ የጠቆሙት ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ እስከ ዛሬ ድረስ ሲከፍል ከነበረው ሁለት እጅ እጥፍ ጭማሪ እንደሚደረግበትም ምንጮቹ ገልፀዋል::

እስከ ዛሬ 100 ብር ሲከፍል የነበረ በአዲሱ ታሪፍ ጭማሪ ከ200 እስከ 300 ብር እንዲከፍል ሊደረግ መሆኑን የጠቆሙት ጥናቱን የተመለከቱ ምንጮች ጭማሪው የማይቀር ቢሆንም ለግዜው የጀመርነው አዲሱ መደናገሪያ ስልት ሊከሽፍብን ይችላል በሚል ለሁለት ወራት እንዲራዘም መደረጉንም ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በአሁኑ ሰዓት የመብራት ታሪፍ ጭማሪ ማድረጉ በአባይ ላይ የጀመርነው ቅስቀሳ ሊከሽፍብን ይችላል ....... በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት እንደተጀመረውና እንደተደረገው

የህዝብ ተቃውሞና አመፅ ሊያስነሳብን ይችላል በሚል ፍርሀት ለሁለት ወር እንዲዘገይ የመብራት ኃይል ባለስልጣኖችን ማዘዙንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ከሁለት ወር በፊት የመብራት ኃይል መስሪያ ቤት በአስቸኩዋይ የዋጋ ጭማሪውን ጥናት አድርጎ እንዲያቀርብለት በመለስ ዜናዊ ፊርማ የወጣ ደብዳቤን መሰረት አድርገው ጥናቱን ያቀረቡ ቢሆንም ወቅቱ ለወያኔ አስቸጋሪ በመሆኑ እንዲራዘም ተደረገ እንጂ ጭማሪው የማይቀር መሆኑን ምንጮቹ አጽንኦት ሰጥተው ገልፀዋል፡፡

በነዳጅ ጭማሪ ፤በኑሮ ውድነት፤ በማህበራዊና በፖለቲካ ችግሮች ተወጥሮ ያለውን ህዝብ እንደገና ይባስ ብለው በውሀ ታሪፍ ላይ ጭማሪ ማድረጋቸው ሳያንስ አሁን ደግሞ በመብራት ክፍያ ላይ ከ200 ፐርሰንት በላይ ለመጨመር መዘጋጀታቸው የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በተያያዘ ዜና ወያኔ ገበያውን አረጋጋለሁ ብሎ የባሰ ኑሮው እንዲያሻቅብ ከማድረጉም በተጨማሪ የሸቀጦች እጥረት እንዲያጋጥም ሆነ ብሎ እየሰራ በመሆኑ ህዝቡ ለከፋ የኑሮ ውድነት ተዳርጎዋል፡፡የወያኔ ማዕከላዊ እስታስቲክስ ተብሎ የመጠራው ድርጅት ሳይቀር በተለይ በመጋቢት እና በሚያዝያ ወሮች የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት ተከትሎ ከ25 በመቶ በላይ የእቃዎች ዋጋ እንዲንር ምክንያት መሆኑን ጠቁሞ አሁን ባለው ሁኔታ የሚቀጥል እንጂ የሚቀንስ አለመሆኑን በይፋ አምኖ ገልፆዋል፡፡

ገበያ አረጋጋለሁ ብሎ ነጋዴውን ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ ባዘጋጀው እቅድ መሰረት ኢት ፍሩትና ጅንአድ በተባሉ ድርጅቶች እቃ እያቀረብኩኝ ነው ቢልም ለህዝቡ የሚደርስ አንድም ሸቀጥ የሌለ በመሆኑ ህዝቡ ጠዋት ወጥቶ ተሰልፎ ማታ ባዶ እጁን እየተመለሰ ለአሳዛኝ የኑሮ ምስቅልቅል ተዳርጎ ይገኛል፡፡

የወያኔ ነባር አባል የሆኑና ከትግል በጡረታ የተሰናበቱ ከህዝቡ አፍ ላይ እየነጠቁ ከጅንአድ በምስጢር እያወጡ በጥቁር ገበያ በእጥፍ እያተረፉ እየሸጡ ሲሆን ለዋጋው ማሻቀብ አይነተኛ ሚና እየተጫወቱ ከመሆኑም በተጨማሪ ደሀው ህዝብ ግን የፈለገውን እንዳይገዛ አቅም ስለሌለው ጠዋት ወጥቶ በጸሀይ ተቀቅሎ ባዶ እጁን ለመመለስ ግድ ብሎታል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እቃ ጠፍቶ ህዝቡ ከመቸገሩም በላይ እያለቀሰ ቢሆንም እስከ አሁን የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ እንደሌለም ታይቶዋል፡፡

የፋሲካን በዓል ምክንያት ተደርጎ ሰሞኑን ደግሞ እጅግ አስገራሚ የዋጋ ጭማሪ የተደረገ ሲሆን የወያኔ ቡድንም ችግሩን ከመቅረፍ ይልቅ የበለጠ እንዲባባስ በማድረግ ከዚህ ቀደም ከነበረው ግዜ ሁሉ በከፋ ሁኔታ ኑሮው እንዲንር ማድረጉን ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በአግባቡና በተመጣጣኝ ዋጋ ለህዝቡና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዳይዳረስ እራሱ ባደራጃቸው ቀድሞ ታጋይ በሆኑት አሁን በጡረታ በተሰናበቱት ግለሰቦች አማካኝነት ህዝቡን እየመዘበሩና ለከፋ ችግር እየዳረጉት እንደሚገኝ ተረጋግጦዋል፡፡

የአባይ ግድብን እገነባለሁ በሚል የውሸት ፕሮፓጋንዳ ከህዝቡ ላይ በግድ እያስፈራራ ገንዘብ እየሰበሰበ ያለው የወያኔ ቡድን ዜጎች በርሀብና በኑሮ ውድነት እንዲሰቃዩ ከማደረጉም ባሻገር ቀድሞ ከነበረው የኑሮ ውድነት በላይ እንዲንር አድርጎ እድገት እያስመዘገብኩ ነው እያለ በዜጎች ሞት እና ስቃይ እየተሳለቀ መገኘቱም ታውቆዋል::

በምግብ ፤በሸቀጦች፤ በእህልና በሌሎች ላይ ሰሞኑን የተደረገው ጭማሪ በእጅጉ አስደንጋጭ በሆነ መልኩ መናሩ ህዝቡን ለችግር ከመዳረጉም በተጨማሪ ለወደፊቱም ስጋት ውስጥ እንዲወድቅ ያደረገ ሆኖዋል::ይህንን ችግርና መከራ በህዝብ ላይ የጫነው የወያኔ አምባገነን ቡድን ኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ ከፍተኛ ሚና ከመጫወቱም በላይ ነጋዴው ለህዝቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዳያቀርብ ሆን ብሎ እየሰራ መሆኑም ታውቆዋል::

የኑሮ ውድነቱ ከመክበዱ የተነሳ በአፍሪካ ትልቁ የመገበያያ ስፍራ እንደሆነ የተነገረለት የመርካቶ ገበያ የህዝቡ ግርግር እና ትርመስ ቀንሶ ከአዘቦት ገበያም በታች ሆኖ ነው የሰነበተው::

በመጨረሻም ግራ የተጋባው የወያኔ ቡድን እገነባለሁ እያለ ሲፎክርበትና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ሲጠቀምበት በሰነበተው አባይ ስም እየሰበሰበ ባለው ገንዘብ ዙሪያ ተቃውሞ እየገጠመው በመሆኑ ተቃዋሚ መሪዎችን እያስፈራራ መሆኑ ተጠቆመ::

በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ በየሁለት ቀናት ልዩነት የወያኔ መሪዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ ድርጅቱም ተቃዋሚ መሪዎችን የሚያስፈራራ መግለጫ ማውጣቱ ታውቆዋል::

እንዳሰበውና እንዳቀደው ያልተሳካለት የወያኔው ቁንጮ የሆነው መለስ ዜናዊ አስቀድሞ ለሀገር ውስጥ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የተቃዋሚ መሪዎችን እና የወያኔን ቡድን የማይደግፈውን ሰፊ ህዝብ እያስፈራራ በግዴታ የአባይ ግድብን ፕሮጀክት መደገፍ እንዳለባቸው ቢያስጠነቅቅም አድማጭ ባማጣቱ በሁለተኛው ቀን እንደገና በድርጅቱ ስም መግለጫ ማውጣቱ ታውቆዋል::

በዚህ ብቻ ያላቆመው የወያኔ ቡድን እንደገና ለሶስተኛ ግዜ የውጭ ጉዳይና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የወያኔው የከተማ ታጋይ ኃይለማርያም ደሳለኝ የወያኔን መግለጫ ተከትሎ ሐሙስ ሚያዚያ 13 ቀን 2003 ዓ.ም ድንገት ህዝቡን ጭምር የሚያስፈራራና መስጠንቀቂያ የሚሰጥ ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠቱ ታውቆዋል::

በዚሁ በሰጠው መግለጫ ላይ በተለይ የተቃዋሚ መሪዎችን የልማት እንቅፋት .......አፍራሽ ኃይሎች እያለ ሲሳደብ እንደነበርና የአባይን ግድብ የሚቃወም ቢኖር የከፋ ችግር ሊደርስበት እንደሚችል ሲናገርም ተደምጦዋል::

ከአባይ ግደብ በፊት በርሀብ እየሞቱ ያሉ ዜጎቻችንን እናድን ...... በኑሮ ውድነት እየተሰቃዩ ያሉ ወገኖቻችንን ከውጥረት አናስተንፍስ ቢባልም ወትሮም ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ብቻ እየተጠቀመበት

በመሆኑ ምስጢሬ ለምን ታወቀብኝ በሚል ድንጋጤ ሰሞኑን በህዝቡና በተቃዋሚ መሪዎች ላይ ዛቻና ማስፈራሪያ እየሰነዘረ እንደሚገኝ ታውቆዋል፡፡

የአባይ ግድብ ወሬ የወያኔ የማሳሳቻ ፕሮፓጋንዳ መሆኑን እየተረዳ የመጣው ህዝብ ፊቱን በማዞሩ የተደናገጠው የወያኔ ቡድን በተቃዋሚ መሪዎች ላይ ዛቻ ከመሰንዘሩም በላይ ማስጠንቀቂያ እየሰጠ ይገኛል፡፡

በተለይ ይሄው የከተማ ታጋዩ ኃይለማርያም ደሳለኝ እንደገለፀው ከሆነ የአባይ ግድብን ለመገንባት ጥናት የተደረገው አሁን ሳይሆን በ1956 ዓ.ም በአፄ ኃይለስላሴ ግዜ እንደነበር አምኖ መናገሩ አስገራሚ ሆኖዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የኑሮ ውድነቱ ከርሮ ውል አልባ በሆነበትና ህዝቡ እየመረረው በመጣበት በዚህ ግዜ...... ከውጭ የአፍሪካ ህዝቦች የአምባገነን መሪዎቻቸውን የግፍ አገዛዝ በቃን ብለው አመፅ አንስተው በማሽቀንጠራቸው የተደናገጠው ወያኔ ለግዜያዊ ስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ይሆነኛል በሚል ስሌት ብቻ ያለ ምንም ጥናት በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ የአባይ ግድብን እገነባለሁ ብሎ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ እንደነበርና ዛሬ ግን መልሶ ጥናቱን እነሱ እንዳልሰሩትና በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ግዜ የተጠና መሆኑን አምኖ መናገሩ አስገራሚና አነጋጋሪ ሆኖዋል፡፡

ሀገር ሲያፈርስና ሲንድ .......ህዝብን በጎጥና በሰፈር ሲያጋጭና ሲያበጣብጥ.....ለም መሬት ለባዕዳን ሲሸጥ.....ሀገሪቱን ወደብ አልባ አድርጎ ባዶ እጅ ሲያስቀር..... ለ20 ዓመታት ስልጣን ላይ የቆየው ይሄው የወያኔ ቡድን የጀመረው የአባይ ግድብ ፕሮጀክት እውን እንደማይሆን ይልቁንም ለእድሜ ማራዘሚያው የሚሆን ገንዘብ ከህዝቡ ላይ እየሰበሰበ ነው ተብሎ ከፍተኛ ትችት ሲሰነዘርበት የነበረ ሲሆን የተባለው ሁሉ እውን ሆኖ ሰሞኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እቅዱን ወያኔ እንዳላጠናውና የእነሱ እንዳልሆነ በይፋ እራሳቸውን አጋልጦዋል፡፡

ለሀገር እና ለህዝብ ብሎ የማያስበው ይሄው አረመኔ የወያኔ ቡድን ዛሬ ዙሪያ ገባውን ተወጥሮ ሲያዝና መላወሻ መተንፈሻ ሲያጣ ግዜ መግዣ ይሆነኛል.... የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ አደርጋለሁ ብሎ ባለሙያዎች በቂ ጥናት ሳይደረጉበትና ህዝቡ ሳይመክርበት ድንገት በአንድ ጀምበር የአባይ ግድብ ስራ ጀምሬያለሁ እያለ ቢወተውትም ህዝቡ ሳይቀበለው መቆየቱን ተከትሎ ሰሞኑን ደግሞ የተደበቀውን ምስጢር ሊያሾልክ መቻሉ አነጋጋሪ ሆኖዋል፡፡

ከጎንደር ለም መሬቶችን እየቆረሰ ለሱዳን ሲቸበችብ የኖረው ወያኔ.....በጋምቤላ ደኖች ተጨፍጭፈው ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች ሲያከፋፍል የኖረው አረመኔ ቡድን......ዜጎችን በጠራራ ፀሀይ እየገደለ የፍየል ወጠጤን የሚፎክር ዘረኛ ቡድን ዛሬ ድንገት የአባይ ግድብን ልገነባ ነው እያለ ቢፎክር እንዴት ሊታመን ይችላል? ሲሉ የጠየቁት ምሁራኖች ዛሬ በውጥረት ውስጥ ሲገባ ይህችን ዘዴ ተጠቅሞ ሊያልፍ ያዘጋጃት እቅድ እንጂ ለሀገር አስቦ እንዳልሆነም አጽንኦት ሰጥተው ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ወያኔ በአባይ ላይ ጥናት አለማደረጉን ለህዝቡ ጆሮ እንዳይደርስና እንዳያውቅ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም ድንገት ሳይታሰብ ኃይለማርያም የተባለው የከተማ ታጋይ የወያኔን

ገመና በማጋለጡ እውነታው ይፋ የወጣ ሲሆን አሁንም ይሄንን ፕሮጀክት የማይደግፍ ቢኖር የከፋ እርምጃ እንደሚወሰደበትም ጭምር ማስጠንቀቁም ታውቆዋል፡፡